ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ
Forum for Social Studies(FSS)

ህዳር 2013 የፖሊሲ ፍሬ ኃሳቦች ቁጥር 43

# የሴቶች የመሬት ባለቤትነት፣ አጠቃቀም እና መብት ሁኔታ በኢትዮጵያ

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ በሀገሪቱ የልማት ችግሮች ዙሪያ ፖሊሲ ነክ ምርምሮችን የሚያካሂድ ለትርፍ ያልተቋቋመ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ነው።

♣ ♣ ♣

የምርምር ውጤቶቹን ለፖሊሲ አውጪዎችና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሱ ያደርጋል፣ ሕዝባዊ ውይይቶችን ያዘጋጃል፣ የተለያዩ የሕብረተሠብ ክፍሎችን ኃብዞ ያወያያል።

♣ ♣ ♣

በድረ-ገጹ የሕትመት ውጤቶቹን ዝርዝር ያቀርባል፣ በልማት ዙሪያ ውይይቶችንም ያካሄዳል።

♣ ♣ ♣

በርዕሱ ዙሪያ ኃሳብ መሰንዘር የምትፈልጉ በኢሜል አድራሻችን ላኩልን።

♣ ♣ ♣

ኢሜል፡ fss@ethionet.et

ድረ-ገጽ፡ www.fssethiopia.org

## መግቢያ

በአብዛኛው በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት ውስጥ ያሉ ሴቶች መሬት የማግኘት እና የመጠቀም መብታቸው ከወንዶች አንፃር ሲታይ በጣም ዝቅተኛ ሆኖ ይገኛል። በተለያዩ ፖሊሲዎች የሰፈረው የሴቶች ሀብት የማፍራት ወይም የማግኘት እና በሀብቱ የማዘዝ መብት ትግበራ አለመከበር የሚጀምረው ራሳቸው ሴቶቹ ከሚኖሩበት ቤተሰብ እና ማሕበረሰብ ሲሆን ይህም ሴቶችን ለተለያዩ ተግዳሮቶች ሲዳርጋቸው ይስተዋላል። በቤጂንግ ፕላትፎርም ፎር አክሽን ሪፖርት ላይ እንደተገለፀው የሴቶች ድህነት ከገቢ ምንጭ ማነስ እና በገቢው ላይ ከመወሰን አቅም እና ነፃነት፣ እንዲሁም በውሳኔ ሰጪነት ላይ ካላቸው ዝቅተኛ ተሳትፎ ጋር ተያያዥነት አለው።

## የሕግ ማዕቀፎች

በዓለም እና በሀገር አቀፍ ደረጃ ባሉ የፖሊሲ ዶክመንቶች ስለ ሴቶች መሬት እና ሌሎች ተጓዳኝ ሀብቶች በባለቤትነት የመያዝ እና በንብረቱ የመጠቀም መብቶች ተቀምጠው ይገኛሉ። በሀገር አቀፍ ደረጃ በሕገ-መንግስቱ፣ በኢትዮጵያ ሴቶች ፖሊሲ፣ የኢትዮጵያ ሴቶች ልማት ፓኬጅ እንዲሁም በፌዴራል እና ክልል የመሬት አጠቃቀምና አስተዳደር አዋጆች ላይ ሴቶች ከወንድ አቻዎቻቸው ዕኩል መሬት የማግኘት፣ በንብረቱ የመጠቀም፣ የማዘዝና የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የማግኘት መብት እንዳላቸው ደንግገዋል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ በዘላቂ ልማት ግብ 2016-2030 ላይ ከተቀመጡት ግቦች አንዱ የስርዓተ ፆታ እኩልነትን ማረጋገጥ እና ሴቶችንና ልጃገረዶችን ማብቃት ሲሆን፣ የቤጂንግ ፕላትፎርም ፎር አክሽን ዶክመንት ላይም ሴቶችን ለማብቃት እና ለቀጣይ ደረጃ መሻሻል ይረዳ ዘንድ ውርስን ጨምሮ የሚያስፈልጋቸውን ሀብት በእኩልነት ማግኘት የሚችሉበትን መንገድ ማረጋገጥ እንደ አንድ እርምጃ አስቀምጧል። ይህንም ለማሳካት ይረዳ ዘንድ መንግስታት አስፈላጊውን የሕግ እና የአስተዳደር ማሻሻያ እንዲያደርጉም ተጠቅሷል።

## የሴቶች የመሬት ይዞታ ሁኔታ በኢትዮጵያ

የመሬት ይዞታ ማለት በአንድ መሬት ላይ የመጠቀም፣ የባለቤትነት ስም የማግኘት፣ ለመሸጥም ሆነ ለማከራየት የውሳኔ ሀሳብ የማስተላለፍ ስልጣንን የሚያካትት ነው። በአብዛኛው ማሕበረሰብ ውስጥ የመሬት አስተዳደር ጉዳይ በግልፅ በተፃፉ እና ከማሕበረሰቡ በተወጣጡ የጋራ ዕሴቶች፣ ባሕሎችና ልማዳዊ ደንቦች ይዳኛል። እነዚህ ልማዳዊ ሕጎች ደግሞ ለሴቶች የመሬት ይዞታ መብት የሚሰጡት ቦታ ሁለተኛ ደረጃ ከመሆኑም ባለፈ በቤተሰቡ ውስጥ ባላቸው ቦታ (ሚስት ወይም ልጅ) እንዲወሰኑ ያደርጋሉ።

በኢትዮጵያ ለሴቶች መሬትን የመጠቀም ዕድል ከሚሰጡ ማህበራዊ ተቋማት መካከል አንዱ የሆነው ጋብቻ ነው። በአብዛኛው የአገሪቱ ክፍሎች እንደሚታየው ግን፣ በጋብቻ የሚገኝ የመሬት ሀብት የትዳር ግንኙነቱ እስከቀጠለ ጊዜ ድረስ የሚቆይና ፍቺ ሲከሰት ወይም አባወራው በመሬቱ ዙሪያ ያለው የስራ ፍላጎት ሲቀየር እማወራዋ ከመሬቱ የምታገኘው ጥቅም ሙሉ በሙሉ የሚቋረጡበት ጊዜያቶች ብዙ ናቸው። በሌላም በኩል እናት አቅመአዳም ባልደረሱ ልጆቿ ስም መሬት ብትይዝም ይህ መብቷ ሙሉ በሙሉ ወይንም በከፊል አቅመአዳም በደረሰ ወንድ ልጇ ትነጠቃለች። ይህ በወንድ የዘር ግንድ ላይ የተመሠረተ የመሬት መብት ማስተላለፍ ስርዓት የሴት ልጆችን መብት የሚገድብ ነው።

## መሬት እና የመሬት አስተዳደር

መሬት አስተዳደር ማለት መሬት የማግኘት፣ የመጠቀምና መሬቱን በተመለከተ ውሳኔ የሚሰጥበትና እና መብት የሚተላለፍበት እንዲሁም በመሬት ዙሪያ የሚነሱ ግጭቶች የመፍታት ሂደት የሚከናወንበት መንገድ ነው። የመሬት መብት ማግኘት በሕግ በታወቀ ተቋም የሚሰጥ እውቅና ሲሆን የሴቶችን የመሬት መብት ለመረዳት በመጀመሪያ ሕጋዊ እና ማሕበራዊ መብቶችን እንዲሁም በሕግ ማዕቀፉ እና ሕጉን ከማስፈፀም አቅም መካከል ያለውን ግንኙነት በጥልቀት መረዳት ይጠይቃል።

በ1995 የኢትዮጵያ ሕገ-መንግስት መሬት የኢትዮጵያ መንግስትና ሕዝቦች የጋራ የማይሸጥ የማይለወጥ ሀብት መሆኑን በአንቀፅ 40.2 ተደንግጓል። በዚሁ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 4፣ 5 እና 6 ላይ ደግሞ የኢትዮጵያ አርሦ አደሮች፣ አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለግብርና እና ለግጦሽ የሚውል መሬት በነፃ የማግኘት እና ከዚሁ ይዞታቸው ላይ ያለመፈናቀል መብት እንዳላቸው ተደንግጓል። በተጨማሪም የመሬት አስተዳደር እና ልማት ድንጋጌ 456/2005 ለግብርና ስራ በመሬት የመጠቀም ዘላቂ መብት ሰጥቷል። የመሬት ይዞታን ለማረጋገጥ መብትን ለማረጋገጥም መመዝገብ እና ማረጋገጫ ሰርተፊኬት በመስጠት ማጠናከር እንደሚያስፈልግም ይደነግጋል። የመሬት ይዞታ ማረጋጫ ሰርተፊኬት መኖር ለሴቶች መብት ጥበቃ ያደርጋል ብሎ መንግስት ይሞግታል። ምክንያቱም ይህንን መብት የያዘች ሴት

ከመሬት ውጭ ያሉ እንደ የወንድ ጉልበት እና በሬ የመሳሰሉ ለእርሻ ስራ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ባይኖራትም መሬቷን አከራይታ ወይም ለዕኩል አራሽ ሰጥታ በገቢው መጠቀም ያስችላታል ተብሎ ስለሚታመን ነው።

## የሴቶች የመሬት ይዞታ መብት መረጋገጥ ያለው ጠቀሜታ

የመሬት ይዞታ ማሻሻያ አዋጆች የተለያዩ ዓላማዎችን ለማሳካት ይደረጋሉ። በኢትዮጵያም በፌዴራል ሆነ በክልሎች ደረጃ የወጡት የመሬት አዋጆች ለመሬት ጥያቄ ፍትሀዊ ምላሽ ለመስጠት እና የገጠሩን ማሕበረሰብ የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል ታልመው የወጡ ናቸው። በጥናት እንደታየው በየጊዜው የሚደረግ የመሬት ክፍፍል እና ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚመጣው የይዞታ መተማመኛ ማጣት መሬቱን በአግባቡ ለመጠቀም፣ ለመንከባከብ እና በመሬቱ ላይ ዘላቂ ጥበቃ ለማድረግ ተነሳሽነትን እንደሚቀንስና ለመሬት መጎዳት ለስነ-ምህዳር ቀውስ እና ምርታማነት ማሽቆልቆል ምክንያት እንሚሆን ነው።

የመሬት ይዞታ በፖሊሲው መረጋገጡ እና መተግበሩ የሚከተሉትን አዎንታዊ ለውጦች ማምጣት ይችላል

1. በቂ የኑሮ ፍላጎቶችን ለማሳካት፡- ሴቶች ለራሳቸውም ብሎም ለቤተሰባቸው አስፈላጊውን የዕለት ተዕለት ፍላጎት ለማሟላት እና አስቸጋሪ የሆኑ የሕይወት ተግዳሮቶችን ለመወጣት ይጠቅማቸዋል።

2. የቤተሰብ የምግብ ዋስትናን ለማሳካት እና የስርዓተ-ምግብን ሁኔታን ለማስተካከል

3. የገጠሩን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል፣ ድህ ተኮር ዕድገት ለማምጣት፣ ዘላቂ የመሬት አጠቃቀም ለመተግበር እንዲሁም በሰላም አብሮ ለመኖር አስተዋፅዎ አለው። የመብቱ መረጋገጥ ባለይዞታዎች የመሬቶቻቸውን ልማትን ለመጠበቅ ወጪ ለማውጣት መነሳሳትን በመፍጠር ምርት እና ምርታማነትን ያሻሽላል

4. የገንዘብ አገልግሎት ሰጪዎችን እና የመንግስት ፕሮራሞችን የማግኘት ዕድል ይጨምራል፡፡ እንዲሁም መሬቱን ተመጣጣኝ ጥቅም ሊያስገኝ በሚያስችል መልኩ በአግባቡ ለመጠቀም ያስችላል።

ዘላቂ ልማት እና ኤች. አይ. ቪ/ኤድስን ለመቆጣጠር ከሚካሄደው ትግል ጋር ጥብቅ ቁርኝት አለው። የገጠሯ ሴት ባላት መሬት ለሽያጭ ከሚውል ይልቅ ለፍጆታ የሚውል ሰብል ማምረት ወይም ያገኘችውን ገንዘብ ለቤተሰቡ ምግብ ወጪ ማድረግ የምትመርጥ በመሆኑ፤ የሴቶች የመሬት መብት መረጋገጥ ከቤተሰብ ምግብ ዋስትና ጋር ትስስሩ የጠበቀ ነው።

## የመሬት ይዞታ ፖሊሲ በኢትዮጵያ

የተሻሻለው የ 2005ቱ የመሬት አጠቃቀም እና አስተዳደር አዋጅ አንቀፅ 5/ለ ማንኛውም ዕድሜው 18 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነና በግብርና ሙያ ሊተዳደር የሚፈልግ ዜጋ የገጠር መሬት የመጠቀም መብቱ እንደሚጠበቅ ይገልፃል። በአንቀፅ 5/ሐ. በግብርና ስራ መሰማራት የሚፈልጉ ሴቶች የገጠር መሬት የማግኘትና የመጠቀም መብት እንዳላቸው ሲደነገግግ ይህም ገደብ እንደሌለው በአንቀጽ 7/ሀ ተቀምጧል።

የአብዛኛዎቹ የገጠር ሴቶች የመሬት ይዞታ ጉዳይ ተደራራቢ በሆኑ በዕለት ተዕለት ህይወታቸው ውስጥ ባሉ አግላይ የሆኑ የማሕበረሰቡ ተግባራት፣ ፈጣን ምላሽ በማይሰጠው የሕግ ስርዓት፣ የኢኮኖሚ እና ውሳኔ ሠጪነት አቅም ማጣት የተተበተበ ነው። የሚወጡ ፖሊሲዎችና አዋጆች እነዚህን ጉዳዮች ከግምት ውስጥ ባለማስገባታቸው ምክንያት የሴቶች የመሬት ይዞታ መብት ሲጎደል ይታያል። ይሁን እንጂ የአለም ባንክ በ2008 ባካሄደው ጥናት መሰረት በኢትዮጵያ ያለው የመሬት ምዝገባና ሠርተፊኬት የመስጠት ሂደት እንዲሁም በሠርተፊኬቱ ላይ የሴቶቹ ስምና ፎቶግራፍ እንዲካተት መደረጉ ቀላል ነገር ግን ውጤታማ በሆነ መንገድ የሴቶቹን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ደረጃ ማሻሻሉን አመልክቷል።

## የመሬት ይዞታ ፖሊሲ አፈፃፀም እና ሰርተፊኬት አሰጣጥ ሂደት

ኢትዮጵያ በመሬት ዙሪያ ሕጋዊ እና ተቋማዊ አደረጃጀት ላይ ለውጥ ካደረጉ ሀገሮች መካከል አንዷ ነች። የለውጡ ዓላማም ለነዋሪው የይዞታ መብት አዲስና የተሻለ ጥበቃ መስጠት፣ የመሬት መብትን በተመለከተ የየአካባቢው ሰዎች ማስተዳደር እንዲችሉ ማድረግ፣ የግጭት አፈታት ስርዓት እና የሴቶችን የመሬት መብት ሁኔታ ማሻሻል ነበር። ይህንኑ ዓላማ ይዘው በክልሎች የመሬት አስተዳደር የመሬት መጠቀም መብት ለሁሉም ገበሬዎች ሰርተፊኬቱን በተመጣጠኝ ዋጋ ለመስጠት ተቋቁመዋል።

በመሬት አስተዳደሩ አዋጅ 456/2005 አንቀፅ 17 1 እና 2 ላይ እንደተገለፀው እያንዳንዱ የክልል ምክርቤት ዝርዝር ድንጋጌዎችን የያዘ የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም ህግ እንዲያወጡ እና ይህንን ስርዓት የሚያስፈፅሙ ድርጅታዊ ተቋሞች በተዋረድ እንዲያቋቁሙ እንዲሁም የተቋቋሙትም እንዲጠናከሩ ማድረግ እንዳለባቸው አስቀምጧል። በተጨማሪም ሕገመንግስቱ 52/2/መ ለክልል መንግስታት መሬትን እና ሌሎች የተፈጥሮ ሀብትን የማስተዳደር ስልጣን ይሰጣቸዋል።

በዚህ በአዲሱ የመሬት አዋጅ አንዱ ዋና ፍሬ ጉዳይ ተደርጎ የተያዘው የመሬት ምዝገባ ሰርተፊኬት ሲሆን የመሬት መብት ምዝገባ ማለት የአንድን መሬት ባለይዞታ ማንነት እና የይዞታውን አይነት የሚገልፅ ነው። ይህ ምዝገባ ሂደት በመሬቱ ላይ ያለውን መብት የማግኘት እና ለማጣት መተማመኛ መሠረት የሚጥል ነው። የመሬት ሰርተፊኬት የተወሰነ መብት ለባለ ይዞታው ያጎናጽፋል። ከነዚህ መካከል መሬቱ በልማት ቢወሰድበት በመሬቱ ላይ ላለማው ንብረት የካሣ ክፍያ መጠየቅ፣ በመሬቱ ላይ ያለውን የመጠቀም መብት የማስተላፍና በጊዜ ገደብ መሬቱን ማከራየትን ያካትታል። ምንም እንኳን የመሬት ሰርተፊኬት ማግኘት የተሟላ የይዞታ መብት ባይሰጥም የመሬት ዕጥረት እየተባባሰ ባለበት እና የይዞታ ባለቤትነት ችግር ለረጅም ዓመታ ሠፍኖ በቆየበት ጊዜ የመጣ በመሆኑ ቀላል የማይባል መሻሻሎችን አስመዝግቧል።

በአገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች እንደታየው ከሆነ የመሬት ምዝገባና ሰርተፍኬት አሰጣጥ ፕሮግራም ሂደት የሚጀመረው ከአካባቢው ህዝብ ጋር በሚደረግ ስብሰባ ላይ በአብላጫ ድምፅ በሚመረጡ 12 አባላት ባሉት የመሬት አስተዳደር ኮሚቴ ሲሆን፤ ለኮሚቴ አባላቱ ስለፕሮግራሙና አተገባበሩ የሁለት ቀናት ስልጠና ይሰጣቸዋል። ስራው ቤት ለቤት በመዘዋወር የሚከናወን ሲሆን መረጃው ሲጠናቀቅ ግልፅነትን ለመጨመር እና ስህተትን ለመቀነስ የህዝብ ውይይት ከተደረገበት በኂላ በመዝገብ ተመዝግቦ፣ ስም እና ፎቶ ያለው የመጀመሪያ ደረጃ ሰርተፊኬት ለቤተሰቡ ይሰጣል። ይህ የመጀመሪያ ደረጃ ሰርተፊኬት አሰጣጥ ሂደት ፈጣን፣ አነስተኛ ዋጋ የሚጠይቅ ፣ ለማንም ያላደላ እና በሕዝብ በተመረጡ ኮሚቴዎች የተመራ ነበር።

ምንም እንኳን ይህ የአሰራር ሂደት ጠንካራ የሕዝብ ተሳትፎ በማረጋገጥ በኩል ጠቃሚ ሚና እንዳለው ቢታመንም በአብዛኛው የአፈፃፀም ሂደት ላይ እንደታየው ግን በኮሚቴ አወቃቀሩም ሆነ በአጠቃላይ አፈፃፀሙ የሴቶች ተሳትፎ ደካማ ሆኖ ተገኝቷል።

የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት እደላ በኢትዮጵያ ከ1998 ዓ.ም. ጀምሮ የተካሄደ ሲሆን በሂደቱም ከ5 ሚሊዮን በላይ ሰርተፊኬት ተሰጥቷል። ምንም እንኳን የተመዘገቡት ውጤቶች ከክልል ክልል ቢለያዩም በአጠቃላይ ውጤቱ የሚያነቃ ሆኖ ተመዝግቧል። በትግራይ 88 ፐርሰንት የገጠር ነዋሪው ሰርተፊኬቱን በ1998 እስከ 1999 በተካሄደው

ምዝገባ ተቀብለዋል። በአማራ ክልል ምዝገባውን ሙሉ በሙሉ በሦስት ዓመት ለማጠናቀቅ ታቅዶ በሁለተኛው ዓመት መጨረሻ ላይ 79 ከመቶ መጠናቀቁን ሪፖርት ተደርጓል። በኦሮሚያ ከሚጠበቀው 4.1 ሚሊዮን ውስጥ የ2.5 ሚሊዮኑ መረጃ የተሰበሰበ ቢሆንም ሰርተፊኬቱን የማደል ስራ ላይ ባገጠሙ የሰው ሀይልና እና የበጀት እጥረት ችግሮች ምክንያት መዘግየት ታይቶበታል። በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልል ውስጥ ስራውን ሙሉ በሙሉ 1.8 ሚሊዮን ለሚገመት ቤተሰብ በሁለት ዓመት ግዜ ውስጥ ለማጠናቀቅ ቢታሰብም ከአንድ ዓመት በኂላ 40 በመቶ መረጃ ተሰብስቦ የተጠናቀቀ ሲሆን፤ በኦሮሚያ ክልል እንደታየው ሰርተፊኬቱን የማድረስ ተመሳሳይ ችግሮችም እንደነበሩ ታውቋል።

## ለሴቶች ይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት አሰጣጥ እና ሂደት በተለያዩ ክልሎች

በአራቱ ክልሎች (አማራ፣ ትግራይ፣ ኦሮሚያ እና ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች) የመሬት ምዝገባ እና ሰርተፊኬት አሰጣጥ ሂደት ላይ የተደረገ ጥናት እንደሚያመላክተው በክልሎቹ መካከል በአፈፃፀም ሁኔታ መመሳሰልም ልዩነትም ይታያል። በመጀመሪያዎቹ የስራው ሂደት የማሕበረሰብ ተሳትፎ ማካተቱ፣ ሂደቱ የሚከናወነው ባልተማከለ መንገድ መሆኑ፣ ለመሬት አስተዳደር ኮሚቴዎቹ በሚሰጡት አጭር ስልጠና እና ኮሚቴው አገልግሎቱን የሚሰጠው በነፃ መሆኑ ክልሎቹን ያመሳሰሉዋቸው ዋና ነጥቦች ናቸው። በሌላ በኩል በአማራ፣ ኦሮሚያ እና ደቡብ ክልል ብሔር ብሔረሰቦች ሰርተፊኬቱ በባልና ሚስት ስም በጋራ እንዲሰጥ ቢታሰብም በኦሮሚያ በሰርተፊኬቱ ላይ የተዘጋጀው የአንድ ሰው ፎቶ መለጠፍያ በመሆኑ እና ሰርትፊኬቱ በአንድ ሰው ስም ብቻ በመሰጠቱ ክልሉን ከሌሎቹ የተለየ እንዲሆን አድርጎታል። ለምሳሌ በአማራ ክልል አጠቃላይ ከተሰጡት ሰርተፊኬቶች መካከል በወንዱ ስም ብቻ የወጡት ዘጠኝ ከመቶ ሲሆኑ በኦሮሚያ ግን 58 ከመቶ ሆኖ ተገኝቷል።

በአሰራሩ ላይ በመሬት አስተዳደር ኮሚቴ ውስጥ የሴቶች ውክልና አናሳ እንደሆነ ጥናቶች አመልክተዋል። በሁሉም ክልሎች ከተመሰረቱ ኮሚቴዎች መካከል 20 ከመቶ የሚሆኑት ብቻ የሴት አባል ያካተቱ ሲሆን በኦሮሚያ ክልል ሴት የኮሚቴ አባላት የያዙት ስምንት ከመቶ ሆኖ ተገኝቷል። ትግበራው በየክልሉ ያመጣው ውጤት ሲገመገም አካባቢያዊ፣ ማሕበራዊ እና ባሕላዊ ሁኔታዎች ተፅዕኖ እንደነበራቸው ታይቷል። በትግራይ ያሉ ሴቶችን ብንወስድ በአዋጁ መሠረት ሴቷ ከወንድ አቻዋ እኩል መሬት ያገኙ ሲሆን መሬት በየግላቸ የሌላቸውም ቢሆኑም ከትዳር አቻቸው እኩል በመሬቱ ላይም ሆነ በምርቱ ላይ የመወሰን መብት ነበራቸው። ባለትዳር ሴቶችም በፍቺ ወቅት የሀብቱን ግማሽ ይወስዱ እንደነበር ጥናቶች አሳይተዋል። በዚሁ ክልልም የባለትዳሮች ይዞታ የሚመዘገበው በወንዱ ስም ብቻ ሆኖ ተገኝቷል። እማወራ የሆኑ ሴቶች መሬት ቢኖራቸው እንኳን ለግብርና ስራ የሚያስፈልጋቸው ጉልበት ስለማይኖራቸው መሬታቸውን ለእኩል አራሽ መስጠት ወይም በተለየ ሁኔታ ጉልበት ሰራተኛ ቀጥረው ማሰራት ይኖርባቸዋል። ይህም ከይዞታቸው ሊያገኙ ከሚገባቸው ጥቅም አናሳ ያደርገዋል።

በአማራ ክልል የሚኖሩ ሴቶችን ስንመለከት በአዋጁ ምክንያት የሀብት እኩሌታ ባለቤት ለመሆን በመቻላቸው በመሬት ዙሪያ ለሚነሱ ግጭቶች እንዲረግብ፣ ገበሬው የተሻለ ምርት እንዲያመርት፣ እንዲሁም ቋሚ የሆኑ እና ሌላ መሬቱን የሚያሻሽሉ ስራዎችን ከበፊቱ በተሻለ ሁኔታ እንዲተገብሩ እንደረዳቸው ጥናቶች አሳይተዋል። ነገር ግን በክልሉ ያሉ እማወራ ሴቶች፣ አካል ጉደተኞች እና አቅመ ደካሞች በመሬታቸው ላይ ራሳቸው መስራት ስለማይችሉ እንዲሁም ለዕኩል አራሽ ለመስጠትም መተማመኛ ስለማያገኙ (ተከራዮቹ በስማቸው ሊያስመዘግቡት ይችላሉ በሚል ፍራቻ) ውጤታማ ሳይሆኑ ሲቀሩ ታይተዋል። በተጨማሪም በፍቺ ወይም በውርስ መብት ጥያቄ ሂደት ላይ ያለች ሴት ሂደቱ ረጅም ስለሆነና መሬቱ አንዴ ከተመዘገበ በኂላ የተሻሻለ ሰርተፊኬት ለማውጣት አስቸጋሪ ስለሚሆን መብቷ አደጋ ላይ የወደቀ ነው። ሴቶች የመሬት መብታቸውን ለማስከበር የባህልና የህግ ተገዳሮቶችም በስፋት ተስተውለዋል። መብቷን የምትጠይቅ ሴት በማህበተሰቡ ውስጥ እንደ ችግር ፈጣሪ በመታየቷ፣ የመደበኛው የፍትህ ስርዓት ለሴቶች በቀላሉ ተደራሽ ባለመሆኑና ጊዜና ገንዘብ የሚጠይቁ በመሆናቸው፤ አብዛኛዎቹ የሴቶች ጉዳይ መደበኛ ባልሆነው በሽማግሌዎች ስርአት እንዲፈታ ይገደዳሉ። በሂደቱም የሴቶቹ ጥያቄ ተደባብሶ ይታለፋል። በዚህም ሴቶቹ በሕግ ከተቀመጠላቸው በታች ጥቅም እንዲያገኙ ተደርገዋል።

በአንዳንድ የአማራ ክልል አካባቢዎች መሬት ያላቸው ሴቶች መሬታቸውን ለማን ለዕኩል እርሻ መስጠት እንዳለባቸው ለመወሰን የሚያስችላቸው ሙሉ ነፃነት የላቸውም። በምስራቅ ጎጃም እና በወሎ የተደረገ ጥናት እንዳመለከተው ባለመሬት ሴቶች መሬታቸውን ለባላቸው ወገን የእኩል አራሽ ወይንም ኪራይ ለመስጠት ይገደዳሉ። ተቀባዩ የባል ወገን ውጤታማ ባይሆንም እንኳ ሴቶቹ መሬቱን ተቀብለው ለሌላ ለመስጠት ይቸገራሉ። በዚህም ከመሬቱ ማግኘት የሚገባቸውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ሲያጡ ይታያል። ምንም እንኳን ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች ለሴቶቹ አዳጋች እየሆኑ መምጣታቸው እውን ቢሆንም የወል ምዝገባ መጀመር ግን በማሕበረሰቡ ውስጥ ላሉ ሴቶች የመብት ማረጋገጫ ሆኖ ተገኝቷል።

በኦሮሚያ ክልል ከባህላዊ አመለካከትና ድርጊቶች ሳቢያ የሴቶች የመሬት ባለቤትነት መብት ሲሸራረፍ ይታያል። በክልሉ ባህል መሬት በቀበሌ ገበሬ ማሕበሩ በሴቷ ስም በተለየ ሁኔታ የተመዘገበ ካልሆነ በስተቀር የመሬት ይዞታ በወንድ ዘር ግንድ በኩል የተያዘና የሚተላለፍ ሀብት ነው። በባህሉ የሴት ልጅ ሀብት ትዳሯ ነው ተብሎ ስለሚታሰብ ሴት ልጅ ከወላጆቿ መሬት አትወርስም። በትዳሯ ውስጥም መሬቱ የበሏ ጎሣ ሀብት እንደሆነ ስለሚቆጠር በፍቺ ወቅት ምንም መሬት አይኖራትም። ይህም የስርዓተ ፆታ ዕኩልነት አለመኖር ማሳያ ከመሆኑ በላይ የሴቶችን የሀብት ባለቤትነት መብትን የሚገድብና ወንድ ላይ ጥገኛ እንዲሆኑ የሚያደርግ ነው። ከባህላዊው ተፅዕኖ በተጨማሪ በኦሮሚያ ክልል ሴቶች መሬት የመያዝ መብት ማጣት ብቻ ሳይሆን በሕግ የተሰጣቸውን መብት በሚገባ ያለመረዳት ችግርም ተስተውሏል። ይሁን እንጂ አዲሱ የመሬት አዋጅ ከተገበረው የመሬት ምዝገባና ሰርተፍኬት ስራ እና የግንዛቤ መጨመር ጋር ተያይዞ ሴቶች መሬትን በተመለከተ ከቅርብ ወዲህ መብታቸውን ለማስከበር ጥረቶች እያደረጉ እንደሆነ ጥናቶች ያመለክታሉ። በአንዳንድ አካባቢዎች አግብተው ከተወለዱበት አካባቢ ርቀው የሄዱ ሴት ልጆችም ከቤተሰቦቻቸው መሬት የድርሻቸውን ለማግኘት ጥያቄ ማቅረብ ጀምረዋል።

በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልል ሴት ለቤተሰቦቿ ጥሎሽ እና ስጦታ በመስጠት ከተዳረች በኂላ የባሏ እና የጎሣው ሀብት እንደሆነች ይታሰባል። ይሁን እንጂ እየተካሄደ ያለው በባልና ሚስት ስም በጋራ የመሬት ይዞታ ሰርተፊኬቱ መሰጠቱ በይዞታው ላይ ያለው መተማመን ከፍ አድርጎታል። በተለይ የሴቶቹ ስም በሰርተፊኬቱ ላይ መስፈሩ ሴቷ ከባሏ ብትፋታ ወይም ቢሞት መሬቱን ይዛ መቀጠል እንደምትችል ያለውን ግንዛቤ አሳድጓል። ሕጉ በመሬት ኪራይ ጊዜ የቤተሰቡ ስምምነት እንዲገለፅ ስለሚጠይቅ እና የኪራዩ ስምምነቱ በቀበሌ ማስመዝገብ ስላለባቸው የትዳር አጋሮችን ስምምነት መጠየቅ ግድ ሆኗል። ይሁን እንጂ በባህላዊ ምክንያቶች አሁንም በውሳኔ ሰጪነት ላይ ጠንካራ የወንድ የበላይነት በመኖሩ ምክንያት ግንዛቤው ያስከተለው ተግባራዊ ለውጥ ውስን እንዲሆን አድርጎታል። ምንም እንኳ ሕጉ ለሴቶች እኩልነትና መብት እውቅና ቢሰጥም ጎጂ ባሕላዊ ድርጊቶች እና ለሴቶች በሚሰጠው ዝቅተኛ ግምት ሳቢያ የሴቶች መሬት የመያዝ እና የመቆጣጠር መብት አሁንም ተገድቦ ይገኛል።

## የለውጡ ማነቆዎች

ሴቶች መሬትን እና ሌሎች የሀብት ምንጭ የሆኑ ንብረቶችን የማፍራትና የመቆጣጠር አቅምን እንዳያጎለብቱ ማነቆ ከሆኑት ነገሮች መካከል በአገር አቀፍና በአካባቢ ደረጃ በቂ የሆነ የሕግ ማዕቀፍ አለመኖር፣ የሕግ በአግባቡ አለመተግበር፣ አግላይ የሆኑ ባሕላዊ አስተሳሰቦችና ድርጊቶች፣ የሴቶች ንቁ ተሳትፎ መገደብ እና የሴቶችን እኩልነት ለማረጋገጥ የአስፈፃሚው አካል ቁርጠኝነት አናሳ መሆን በዋናነት ይጠቀሳሉ።

ከላይ የተጠቀሱትን አበይት ተግዳሮቶች ለመፍታት ያስችል ዘንድ በ2019 አዲስ አዋጅ የተረቀቀ ሲሆን ይኸው አዋጅም በቀደመው ህግ አፈፃፀም ላይ ለሴቶች መብት ተጠቃሚነት ከማረጋገጥ አኳያ አዳዲስ ነጥቦችን አካትቶ ይዟል ይህም ለሴቶች እና ድጋፍ ለሚሹ ሰዎች መብት መጠናከር የሚያስችል ስርዓት ከመፍጠር አኳያም አስተዋፅዖ ይኖረዋል ተብሎ ይገመታል።

## የፖሊሲ ምክረ ሃሳብ

የሴቶችን የመሬት ባለቤትነትና የመጠቀም መብት ይበልጥ ለማስከበር እንዲቻል በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይገባል።

• የስርዓተ ፆታ ጉዳዮችን ማስተዋወቅ፦ ስር የሰደደ የወንድ የበላይነት የሰፈነበትን ስርዓት ለመለወጥ እና የሴቶች እኩልነት እና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በማሕበረሰቡ ውስጥ የአስተሳሰብ ለውጥ ለማምጣት በተለያየ ደረጃ የተቀናጀ ስርዓተ ፆታ ግንዛቤ ማሳደግ ስራ ሊሰራ ይገባዋል። ከዚህም ውስጥ፦

• የመሬት አስተዳደር እና የግጭት ፈቺ ኮሚቴ አባላት በሕግ ዙሪያ ያላቸውን ዕውቀት ማጠናከር እና የስርዓተ ፆታ ጉዳዮች ላይ ያላቸውን ግንዛቤ ከፍ ማድረግ፤

• የሴቶች የመሬት መብት እና አስፈላጊነቱ ጋር በተያያዘ ማሕበረሰቡን የሚያነቁ ጠንካራ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ለሚመለከታቸው አካላት (ሴቶች ራሳቸውን ጨምሮ) መስጠት።

• ሴቶችን የማብቃት ስራ፦ ሴቶችን በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካና ማኅበራዊ ዘርፎች አቅማቸውን ማሳደግና ማብቃት የስፈልጋል። ይኸም መረጃ ማሰራጨት፣ የሴት ማሕበራትን ማደራጀት እና ማንቀሳቀስ፣ ሴቶቹን እና ወንዶቹን ማስተማር፣ የሕግ ድጋፍ በመስጠት፣ ሴቶችን ማገዝ እና ከወንዱ እኩል ጀረጃ እንዲደርሱ ማስቻልን ያካትታል። በዚህም፦

• ሴቶቹ እንዲበቁ እና መብታቸውን መጠየቅ እንዲችሉ የሕግ ዕውቀታቸውን ማሳደግ እና ውጤታማ የሆነ የሕግ ድጋፍ ማድረግ።

• ሴት ገበሬዎች ከግብርና ውጪ ያሉ ገቢ የሚያስገኙ ስራዎች ላይ መሰማራት እንዲችሉ እና ከመሃይምነት ችግር ለማላቀቅ መሰረታዊ ትምህርት እና የሙያ ስልጠና መስጠት።

• በማሕበራዊ ፍትህ ስርዓት አሰራር ውስጥ ለማሳተፍ ምቹ ሁኔታ መፍጠር እና ለሴቶች መብት መከበር ድጋፍ እንዲያደርጉ ማስቻል።

• የሴቶች ተግባራዊ ተሳትፎ ማሳደግ፦ ከመሬት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ላይ እና ግጭት መፍታት ሂደት ውስጥ ሴቶች እና ወንዶች ተሳትፎ ማድረጋቸው የመሬት መብት ለማረጋገጥ ያላቸውን ቁርጠኝነት ለማግኘት ያስችላል። በመሆኑም፦

• በቀበሌ ደረጃ በሚቋቋሙ የመሬት አስተዳደር ኮሚቴ ውስጥ የሴቶችን ውክልና ማረጋገጥ፤

• የፖሊሲ ትግበራውን ውጤታማነት መከታተል፤

• መንግስት የፖለቲካ ቁርጠኝነት እና በቂ በጀት መድቦ የወጡ አወጆችችና መመሪያዎች ትግበራ ሊገመግም እና አስፈላጊውን እርምት በማድረግ የተነሳበት ዓላማ መሳካቱን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል።

## ማጠቃለያ

• በኢትዮጵያ ሴቶች በኢኮኖሚው ዘርፍ ያላቸው ተሳትፎ ዝቅተኛ እና ተጠቀሚነታቸው አናሳ ነው። የመሬት አስተዳደር አዋጆች የሴቶችን መሬት የማግኘት እና የመጠቀም መብት በግልጽ ቢደነግጉም የሴቶች የመሬት ችግር አጥጋቢ በሆነ መልኩ ተፈትቷል ለማለት ግን አያስደፍርም።

• በመሬት እና ስርዓተ-ፆታ ዙሪያ ያሉ ጥናቶች እንደሚያሳዩት በከፍተኛ የመንግስት ዕርከን ደረጃ የተቀመጡት የመንግስት የለውጥ ዕሳቤዎች በታችኛው የአስተዳደር ዕርከን ትግበራ ሂደት ላይ ከልማዳዊ አስተሳሰቦችና፣ ተቋማት እና ፍላጎቶች ጋር ሲጋጩና ተጨባጭ ውጤት ለማምጣት ሲቸገሩ ይስተዋላል። በመሆኑም የአካባቢ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለመቀየር ሕግ ማውጣት የመጀመሪያ ነጥብ ቢሆንም ተግባራዊ ማድረጉ ግን ትልቅ ትግል የሚጠይቅ ነው።

• የወንዶች በመሬት ዙሪያ ውሳኔ መስጠት ላይ ያላቸውን የበላይነት ባሕል መቀየር ጊዜ የሚወስድ ጉዳይ ቢሆንም፤ ለባልና ሚስት በጋራ የመሬት ይዞታ መብት መስጠቱ ጠቃሚ እርምጃ ነው። በመሬት ምዝገባው ዙሪያ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ሂደቱ ሴቶችን የመሬት የማግኘትና የመጠቀም መብት መሻሻል ላይ አዎንታዊ ለውጥ ማምጣት መቻሉን ነው። የሴቶች መሬት የማግኘት፣ የመቆጣጠርና የመጠቀም መብት በሕግ ብቻ የሚወሰን ባለመሆኑ የማሕበረሰቡ ማሕበራዊና ባሕላዊ ልማዶች ላይ የተመሰረተው የስርዓተ ፆታ ግንኙነቱ ከፍተኛ ጫና ሊደረግበት ይገባል ።

• የመሬት ምዝገባውና ሰርተፊኬቱ በራሱ የመጨረሻ ግብ ሳይሆን፤ ፍትሀዊነትን ለማረጋገጥ፣ በገጠሩ የኑሮ መሻሻል ለማምጣት እና ዘላቂ የገጠር ልማት ለማረጋገጥ እንደ አንድ መንገድ የተወሰደ ሆኖ መታየት አለበት። ውጤቱ በግብርናው ዘርፍ ካስገኘው የካፒታል ፍሰት እና የምርት መሻሻል እንዲሁም ያመጣቸው ፍትሃዊ የሀብት ድልድል አኳያ መገምገም ይኖርበታል። በዚህ ረገድ ካሉት ተግደሮቶች ውስጥ የስርዓተ ፆታ እኩልነት አለመኖር እና የሴቶች ተሳትፎ አናሳ መሆን ወይም ከነጭርሱ መጥፋት ናቸው። በመሆኑም በነዚህ ጉዳዮች ላይ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ሊሰሩ ይገባል።

**በመሳይ ያሬድ**

ምንጭ፦ መሳይ ያሬድ (2012) የሴቶች የመሬት ባለቤትነት እና አጠቃቀም መብት ሁኔታ

ምስጋናና ማሳሰቢያ

ይህ የፖሊሲ ፍሬ ሀሳብ የታተመው የኦፕን ሶሳይቲ ኢኒሼቲቭ ፎር ኢስተርን አፍሪካ (Open Society Initiative for Eastern Africa) የገንዘብ ድጋፍ ነው በዚህ ህትመት ውስጥ የተገለጹት አስተያየቶች የፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ የሥራ አመራር ቦርዱን፣የድርጅቱን አጋሮችና የገንዘብ ድጋፍ የሠጠውን የኦፕን ሶሳይቲ ኢኒሼቲቭ ፎር ኢስተርን አፍሪካ (Open Society Initiative for Eastern Africa) አቋምና አመለካከት ላያንጸባርቅ ይችላል።

§§ አድራሻ፦ ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ (FSS) §§ ፖ.ሣ.ቁ.፦ 25864 ኮድ 1000 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

§§ ስልክ፦ 011154 56 05/06 §§ ፋክስ፦ 011154 56 07 §§ ኢሜል፦ fss@ethionet.et §§ ድረ-ገጽ፦ www.fssethiopia.org